# ወርሓዊ ዜና ሚቲዎሮሎጂ

# Monthly Met. News





የወቅታዊ ትንበያ የምክክር መድረኩ ሲካሄድ

ቅጽ 4 ቁጥር 7 የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

ጥር 2010 ዓ.ም

## ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ያለፈውን በጋ ወቅት የአየር ጠባይ ግምገማና በመጪው በልግ ወቅት የሚጠበቀውን የአየር ጠባይ ትንበያ ደንበኞቹ እና ባለድርሻዎቹ በተገኙበት ይፋ አደረገ

ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ያለፈውን በጋ ወቅት የአየር ጠባይ ግምገማና በመጪው በልግ ወቅት የሚጠበቀውን የአየር ጠባይ ትንበያ ደንበኞቹና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ይፋ ያደረገው ጥር 19-20 ቀን 2010 ዓ.ም አዳማ ከተማ ኢዩ ኢንተርናሽናል ሆቴል የምክክር መድረክ ላይ ነው፡፡

የምክክር መድረኩን በንግግር የከፈቱት የውኃ፣ መስኖና ኤሌትሪክ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ የተከበሩ አቶ ከበደ ገርባ ሲሆኑ፣ ‹‹ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር መሠረት በማድረግ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የተሰጠውን ሀገራዊ ኃላፊነት ለማሳካት ሁለንተናዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ አሁን በሚገኝበት ምዕራፍ ላይ ደርሷል። በተለይም መንግሥት የነደፋቸውን የረጅምና የመካከለኛ ጊዜ ዕቅዶችን ስኬታማ ለማድረግ ኤጀንሲው በርካታ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀር እና በመተንተን በየደረጃው ለሚገኙ ፈጻሚ አካላትና ፖሊሲ አውጭዎች ብሎም ለመረጃ ተጠቃሚዎች በማቅረብ በኩል ውጤታማ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል›› ብለዋል። ሚኒስትር ዴኤታው በመቀጠልም፣

‹‹ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ፣ ደንበኞችና ባለ ድርሻ አካላት እንደየተሰማሩበት ዘርፍ የሚፈልጉትን አገልግሎቶች በጥራት፣ በብዛትና በጊዜ አሟልቶ በማቅረብ በማኅበረ-ኢኮኖሚ ልማት ላይ ቀጥተኛ አዎንታዊ አስተዋጽዖ በማድረግ የተፋጠነ የሀገር ልማትን እውን ለማድረግ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ልውውጥን በመተግበር ግዴታውን ለመወጣት በሚችል መልኩ ተደራጅቶ ተግባራዊ እንስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል።

‹‹ይህ የዛሬው መድረክም የኤጀንሲው አገልግሎት አሰጣጥ ምን እንደሚመስል የሚታይበት እንደመሆኑ መጠን በዓመት ሦስት ጊዜ ለአገልግሎቱ ተጠቃሚዎችና ባለ-ድርሻ አካላት የሚያቀርበው ያለፈው ወቅት ትንበያ ግምገማና የመጪው ወቅት ትንበያ ይፋ የሚሆንበት በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ በተጨባጭ እየታየ ነው›› ብለዋል። ሚኒስትር ዴኤታው ንግግራቸውን ሲያጠቃልሉም፣

‹‹የአየር ጠባይ ተጽዕኖን መቋቋም እንዲቻል የሁሉንም ማኅበረሰብ፣ የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀናጅቶ መሥራትን የሚጠይቅ መሆኑና ኤጀንሲውም ከዚህ አንጻር ኃላፊነቱን ለመወጣት ከፍተኛ ሥራዎችን እየሠራ ቢሆንም የባለ ድርሻና ተባባሪ አካላት እንዲሁም የደንበኞች ሚና እጅግ ወሳኝነት አለው። በመሆኑም፣ ዘርፉ ወደ ላቀ ደረጃ እንዲደርስና በቀጣይነትም መረጃዎቹን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚጠቀሙ ባለ ድርሻ አካላትና ደንበኞች ጋር የጋራ መድረክ መፍጠርና ውይይት በማድረግ አፈጻጸምን መገምገምና ቀጣይ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የውይይት መድረክ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። ስለሆነም የሚቲዎሮሎጂ ዘርፉ የሚገለብትበትን እንዲሁም እናንተ ከዘርፉ የምትጠብቁትን የአገልግሎት ጥራት፣ መሻሻል በሚገባቸው ደረጃ እንዲሻሻሉ ሰፊ ውይይትና ምክክር እንደሚደረግ እምነቴን እገልጻለሁ›› በማለት መድረኩን በይፋ ከፍተዋል።

አቶ ፈጠነ ተሾመ የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር በበኩላቸው ባደረጉት የእንኳን ደኅና መጣችሁ ንግግር፣ ‹‹ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የአየር ጠባይ ክስተቶች በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ሊያሳድሩ የሚችሉትን ተጽዕኖዎች በመከታተልና አስቀድሞ በመተንበይ የደንበኞቻችንንና የባለ ድርሻ አካላትን ፍላጎት ለማርካት አቅም በፈቀደ ሁሉ በመሥራት ላይ ይገኛል። ኤጀንሲው የሚሰጣቸው የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ ተልዕኳችንን በአግባቡ መወጣት እንዲቻል ደግሞ ከባለ ድርሻ አካላትና ከደንበኞች የምናገኘው ግብረ-መልስ እጅግ የሚጠቅመን በመሆኑ በዓመት ሦስት ጊዜ የአገልግሎታችን ተጠቃሚዎችና ባለ ድርሻ አካላት በተገኙበት በዚህ መድረክ የበልግ ወቅት ትንበያን ይፋ ያደርጋል፡፡ በዛሬው ዕለትም ባለ ድርሻ አካላትና ደንበኞቻችን በአገልግሎት አሰጣጣችን ላይ ያላችሁን ማናቸውንም አስተያየት ለመቀበልና የታዩትን ክፍተቶች ለማረም እና ለማስተካከል እንዲሁም የተሻለ ተሞክሮ የምናገኝበት መድረክ እንደሚሆን እምነቴ የጸና ነው›› ብለዋል። አቶ ፈጠነ ንግግራቸውን በመቀጠልም፣

‹‹የበልጉ ወቅት የአየር ሁኔታ ትንበያ ከወቅቱ የአየር ጠባይ ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉት መልካም አጋጣሚዎችንም ሆነ ተፈጥሯዊ አደጋዎችን የሚያመላክት በመሆኑ የሀገራችን ሕዝቦች፣ አስፈጻሚዎችና ፖሊሲ አውጭዎች ተገቢውን ቅድመ-ዝግጅት ለማድረግ የሚያስችልና አቅጣጫ የሚጠቁም በመሆኑ በሁሉም ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት

የሚሰጠው ወቅት ነው። በመጨረሻም ኤጀንሲያችን በየጊዜው በሀገራችን የተለያዩ ቦታዎች ሊፈጠሩ የሚችሉትን የአየር ሁኔታ ገጽታዎችን አስቀድሞ በመተንበይ የቅድመ-ማስጠንቀቂያና የትንበያ መግለጫዎች የሚሰጥ በመሆኑ የአገልግሎታችን ተጠቃሚዎች ይህንኑ መረጃ እንዲጠቀሙና የሚሰጠውን የቅድመ-ማስጠንቀቂያ መግለጫዎችን በቅርበት ክትትል እንዲያደርጉ ማሳሰቢያ ሰጥተዋል።

በዚሁ የሁለት ቀናት የምክክር መድረክ ላይ ከኤጀንሲው የወጣው መግለጫ እንደሚያመለክተው ባለፈው የበጋ 2010 ወቅት የሰሜን ንፍቀ ክበብ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በመጠናከራቸው የዓረብ ምድርን አቋርጦ ወደ አገራችን ሲገባ የነበረው ደረቅና ቀዝቃዛ አየር በብዙ ቦታዎች ላይ የሌሊትና የማለዳው የቅዝቃዜ መጠኑን እንዲጨምር ያደረገ ሲሆን፤ በተለይም በአንዳንድ ደጋማ ቦታዎች ላይ የውርጭ መከሰት እንዳስከተለ ተመልክቷል። በሌላ በኩል ደግሞ ከጥቅምት ወር ጀምሮ እስከ ህዳር አጋማሽ ድርስ ሲስተዋል የነበረው የበጋው ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት በጊዜ ሂደት እየቀነሰ በመሄድ የበጋው ደረቃማ የአየር ጠባይ በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እንደተስተዋለ መረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎችና የምዕራብ አጋማሽ በአብዛኛው አካባቢዎች ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ በተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከመደበኛው በታች ዝናብ እንደነበረ ለማወቅ ተችሏል።

በዚሁም መሰረት ኤጀንሲው ከሰጠው መግለጫ ለመገንዘብ እንደተቻለው የዘንድሮው የበጋ ወቅት ከመግባቱ በፊት የተሰጠው የበጋ የአየር ጠባይ ትንበያ በአብዛኛው ከተስተዋለው የአየር ጠባይ ጋር የተጣጣመ እንደነበር መረዳት ተችሏል።

በሌላ በኩል ደግሞ ኤጀንሲው ለመጪው የበልግ ወቅት ትንበያ የሰጠ ሲሆን፤ በትንበያው መሠረት መጪው በልግ ከመደበኛው በታች በሆነ የትሮፒካል የፓስፊክ የባህር ወለል የሙቀት መጠን (La-Nina) እንዲሁም በሰሜናዊ ህንድ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት (Neutral IOD) ተጽዕኖ ሥር ሆኖ እንደሚቀይ ተጠቁሟል። በመሆኑም በትንበያው መሰረት የበልግ ዝናብ ዋነኛ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቆላማ አካባቢዎች፣ በሰሜን ምሥራቅና በምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች መደበኛና ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የተገለጸ ሲሆን፤ በአንጻሩ የምዕራብ

አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ግን በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ስለሆነም በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ክፍሎች ላይ የዝናብ እጥረት ሊያጋጥም ይችላል።

ስለሆነም ህብረተሰቡ በመጪው በልግ ወቅት የሚጠበቀውን የአየር ጠባይ ግምት ውስጥ በማስገባት፤ በዚህ ወቅት የሚካሄደውን የግብርና ሥራና ሊሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥራዎችን ከባለሙያዎች ጋር በመመካከር በአግባቡ እንዲያከናውን ኤጀንሲው ማሳሰቢያ ሰጥቷል። በተለይም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በአብዛኛው ከመደበኛው በታች  ዝናብ እንደሚኖራቸው ስለሚጠበቅ፤ በተለይም በአብዛኛው በበልግ ወቅት የሚስተዋለውን ተለዋዋጭ የአየር ጠባይን ታሳቢ በማድረግ ህብረተሰቡ በተለይም አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ እንዲጠቀምበት እና  በመጪው በልግ ወቅት ከርጥበት ማነስ ጋር ተያይዞ በሚያካሄደው የግብርናና ሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ  ሥራዎች ላይ ሊደርስ  የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለማስወገድ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ኤጀንሲው ማሣሰቢያ ሰጥቷል።

ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ባዘጋጀው በዚህ የምክክር መድረክ ላይ ከአስራ አንዱም የኤጀንሲው የክልል ሚቲዎሮሎጂ ማዕከላት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተገኙ ሲሆን ዘጠኙም ክልሎች የሚወክሉ ስምንት የክልል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎ ማዕከላት የየአካባያቸውን የበጋ ትንበያ ግምገማ፣ የበልግ ወቅት ትንበያና በተለይ በግብርናው ዘርፍ የሚኖረውን ተጽዕኖ አቅርበው ውይይት ተካሂዶበታል፡፡  ከዚህ በተጨማሪም ሁሉም የክልል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት ትንበያውን በማውረድ በየአካባቢያቸው የሚኖረውን የአየር ጠባይ ትንበያ እንዲያቀርቡ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ በዕለቱም ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተፈጥሮ ሀብት ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከግብርና እና ከትራንስፖርት ቋሚ ኮሚቴ ተወካዮች፣  ከዩኒቨርስቲዎች፣ ከሚዲያ አካላት፣ ከምርምር ተቋማት፣ እንዲሁም ከፌዴራል መንግስታዊ ተቋማት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተጋበዙ ከሁለት መቶ በላይ የሆኑ እንግዶች በምክክር መድረኩ ላይ መገኘታቸው ታውቋል፡፡ በምክክር መድረኩ ላይም 20 /ሃያ/ የጥናት ጽሑፎች ቀርበው ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡


NMA ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ
NATIONAL METEOROLOGY AGENCY
UNDP
Empowered lives. Resilient nations.
gef
በብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የበጋ ወቅት የአየር ሁኔታና ጠባይ አፈፃፀምን ከአገልግሎቱ
ተጠቃሚዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር ለመገምገምና በመጪው በልግ ወቅት ሊከሰት የሚችለውን
የአየር ጠባይ ትንበያን ይፋ ለማድረግ የተዘጋጀ የምክክር መድረክ
ከጥር 19 - 21,2010 ዓ.ም
አዳማ : አዩ ኢንተርናሽናል ሆቴል















## የተቋሙን የጥናትና ምርምር ክህሎት ሊያዳብር የሚችል ስልጠና ተሰጠ

ይህ ስልጠና የተሰጠው ከታኅሳስ 23 እስከ ጥር 2 ቀን 2010 ዓ.ም በአዳማ ከተማ ደንበል ቪው ሆቴል ሲሆን በዚህ ስልጠና ላይ ከሁሉም ክልል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት ሁለት ሁለት ባለሙያዎች እና ከዋና መስሪያ ቤት ከሁሉም የኮር ሥራ ሂደቶች የተውጣጡ ባለሙያዎች የተሳተፉበት ሲሆን ስልጠናውን የሰጡት እጅግ በሙያው ዙሪያ ልምድ እና እውቀት ያዳበሩ ከውጭ ሀገር በመጡት ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች በዶክተር ተፈሪ ደጀኔ ከኖርዌይ በርገን ዩኒቨርስቲ፣ ዶክተር ጉልላት ተፈሪ ከሞንትሪያል ካናዳ /ESCER/ ዩኒቨርስቲ፣ እና ዶክተር ድሪባ ቆርቻ ከFEWS-net መሆኑን መረዳት ተችሏል።

ስልጠናው በዋናነት ያተኮረባቸው ርዕሰ ጉዳዮችም የኤጀንሲውን የመፈፀም አቅም ሊያሳድጉ የሚችሉና የባለሙያዎችን ክህሎት ሊያዳብሩ የሚችሉ እንደ CDO/ Climate Data Operator/, NCO, R-Program እና ተያያዥነት ባላቸው ሞዴሎች (Soft Ware) ዙሪያ ሲሆን እንዲሁም በIPCC ጽንሰ-ሐሳብ ዙሪያ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህም በቀጣይነት የምርምር ባህልን እና በቀጣይነት የባለሙያዎችን የመፈጸም ክህሎትን የሚያሳድግ መሆኑ ተገልጿል። በስልጠናው ሂደትም እስከ አሁንም በተቋማችን Enact data እየተጠቀምን ካለመሆኑ ጋር ተያይዘው በቀጣይነት ይህንን መጠቀም ለመጀመር ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ አፅንኦት ተሰጥቶታል።

በዚህ ስልጠና ላይ የተሳተፉት ባለሙያዎች የስልጠናው ጠቀሜታ የጎላ መሆኑን የገለፁ ሲሆን በአሰልጣኞቹ በኩልም በቀጣይነት ያላቸውን እውቀት በሌሎች የሙያ ዘርፎች ማለትም የትንበያ አቅምን ከማሳደግ አኳያ የተለያዩ Appication ዘርፎች እንደ Hydromet, Agromet, Climate Since ዘርፎች ሲከናወኑ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ልምዳቸውን ለተቋሙ ለማስተላለፍ ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በስልጠናው መጨረሻ ቀን ላይ በመገኘት መልዕክት ያስተላለፉት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ እንዳሉት እንደዚህ ዓይነቱ ስልጠና በኢትዮጵያውያን ዲያስፖራ መሰጠቱ ሙያቸውን እና ዓለም አቀፋዊ ልምዳቸው ለመቅሰም የጎላ መሆኑን በመጥቀስ ሠልጣኞችም ትኩረት ሰጥተው በመሥራት ያገኙትን ክህሎት ወደ ተግባር በመቀየር እስካሁን ያልተነካውን የምርምር ሥራዎች ላይ የተቋሙን የመፈጸም አቅም

ማሳደግ እንደሚጠበቅባቸው በመግለጽ እንደዚህ ዓይነቱ ስልጠናዎች በሌሎች የሙያ ዘርፎችም እየተሰጠ የባለሙያዎችን ክህሎትና ብቃት የማሳደግ ስራ በቀጣይነትም በትኩረት እንደሚካሄድ በመልዕክታቸው ገልፀዋል።









**የጥናትና ምርምር ክህሎት ሥልጠናው ሲካሄድ**